# የድል ፡ በዓል ፡ ፹ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ።

ኢ ህ ሥ አ

[www.slttunhzb.net](http://www.slttunhzb.net) sh1@ttomar.net

# ሠልጡንሕዝብና ።

Democracy | 民主 | जनतंत्र | демократия | Δημοκρατία | דמוקרטיה | دِمُقْراطِي

## ማስታወቂያ

announcement | annonce | إعلان

### የሚያዝያ ፡ 27 ፡ ድል ፡ 80 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ በዓል ፡ አከባበር ።

ሚያዝያ ፡ 23 ፡ ቀን ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።

የዛሬ ፡ 80 ፡ ዓመት ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ሀገሩን ፡ ወሮ ፡ ሊቀማበትና ፡ ነጻነቱን ፡ ሊገፍበት ፡ የመጣውን ፡ የፋሺስት ፡ ኢጣልያ ፡ ጦር ፡ ለዘለቄታው ፡ ድል ፡ የመታበት ፡ ዕለትና ፥ በመላ ፡ ዓለም ፡ የቅኝ ፡ አገዛዝን ፡ ፍጻሜ ፡ ያወጀበት ፡ ታላቅ ፡ ሀገራዊም ፡ አህጉራዊም ፡ መታሰቢያ ፡ በዓል ፡ ነው ።

ቀደም ፡ ሲል ፥ የካቲት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ ባከበርነው ፡ የዐድዋ ፡ 125 ኛ ፡ ድል ፡ በዓል ፥ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ የሥልጣኔ ፡ ላቂያ ፡ ታይቶበታል ፥ የሀገራዊነት ፡ አሸናፊነትም ፡ ተመስክሮበታል ። ዘንድሮ ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ ለ 80 ኛ ፡ ጊዜ ፡ በምናከብረው ፡ የድል ፡ በዓል ፡ ደግሞ ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በሀገሪቱ ፡ በጠፋበት ፡ ግዛታዊ ፡ ኹኔታ ፡ ለጊዜው ፡ ድል ፡ ቢኾንም ፡ እንኳ ፥ ግፍን ፡ "እምቢ!" ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ በመታገል ፥ ፋሺዝምን ፥ ዛሬም ፡ መቼም ፥ በመሥዋዕትነት ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ እንደሚቻል ፡ ማረጋገጫውን ፡ አግኝተንበታል ።

ሠልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፥ ዓመቱን ፡ ሙሉ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ሀገራዊ ፡ የድል ፡ አድራጊነት ፡ በዓል ፡ በተለይ ፡ ለማክበር ፡ ስላቀደ ፥ በጽሑፍ ፡ በድምፅ ፡ በርእይ ፡ በሥዕል ፡ በሌላም ፡ አስተዋፅኦዋቸው ፡ ካከባበሩ ፡ ሊሳተፉ ፡ የሚወዱ ፡ ኹሉ ፥ በእ-ጦማር ፡ አድራሻው ፡ በ ፡—

sh1@ttomar.net

እንዲያደርሱለት ፡ ባክብሮት ፡ ያሳስባል ።

የዝግጅት ፡ ክፍሉ ።